ሰኔ 1999 (13 ጁን 2007)

## በቅሎ አባትሽ ማን ነው ቢሏት ፈረስ አጎቴ ነው አለች

(ከ አያልነሽ) ክፍል 2

በሰብሃት ነጋ አዋጅ ላይ የራሱ ወይም የወያኔ ደጋፊና ካድሬ የሆኑ ሰዎች የጠየቁትና በተለይም ያስቀጣቸው ጉዳይ ምን ነበር? ጠያቂዎችስ እነማን ናቸው? በሚል ነበር የመጀመሪያውን ክፍል ያቆምኩት።

ክፍል ሁለት እነሆ!

የተከበራችሁ አንባቢዎች ሆይ!

ልብ እንድትሉልኝ የምጠይቃችሁ የሰብሃት ነጋን የጭንቀት አዋጅ ሙሉ ለሙሉ ለመተቸ አይደለም የዛሬው ሙከራየ። ይህንን እርስ በርሱ የሚቃረን ነገር ግን ለደጋፊዎቹና ለካድሬዎቹ እንዲደርስ የተፈለገውን አዋጅ፣ ሙሉ በሙሉ እያንዳንዱን ለመተችት ወደፊት በስፊው እመለስበታለሁ። ለአሁኑ ላተኩርበት የፈለኩት በኢትዮጵያ ህልውና ላይ ባነጣጠሩ ዋና ዋና ጉድዮች ላይ ሲሆን፣ ሰብሃት ነጋ ለእነኝህ ተከታዮቹ ሊያስተላልፈው ፈልጎ የተኮሰው ጥይት፣ ወደ ፊት መምዘግዘጉን ስቶ ወደ ኋላ በመሺናት የሰብሃት ነጋን አካል ክፉኛ ቦዳድሶታል። አካሉን እንዴት ቦዳደሰው? እስቲ አብረን እንየው

በሲቪሊት ሩሙ ከተኮለኮሉት ሰዎች የመጀመሪያውን ጥያቄ ለመጠየቅ እድል ካገኘችው እህት ቀጥሎ፣ ሁለተኛው ጠያቂ የጠየቀውን ላቅርብ! ሹም ይባላል። ስሙ የፓልቶክ ኒክ ኔም ይሁን እውነተኛ አላውቅም።

ጠያቂው ሹም እንዲህ ሲል ይጀምራል። አመሰግናለሁ አባመላ! የመጀመሪያዋንም ጠያቂ በስም ጠርቶ ሲያመሰግን ይደመጣል። ጤና ይስጥልኝ አቶ ሰብሃት ነጋ! አጭር አስተያየት አለኝ። ጥያቄዬም አጭር ነው። ይኸውም ቀደም ሲናገሩ "ህገ-መንግስታችን" ከተሸራረፈ፣ ከተቆራረሰ በመጀመሪያ አፋር፣ ትግራይ፣ ኦሮሞ ይሄዳል የሚለውን አመለካከት አልጋራውም። ኢትዮጵያ ከትግራይ ውጭ፣ ትግራይ ከኢትዮጵያ ውጭ ይኖራሉ ብዬ እምነት የለኝም። ኮኒስትቲዩሽኑ ከተሸራረፈ እንዳይሸራረፍ ትግሉ ይቀጥላል የሚል አመለካከት አለኝ። ወደ ጥያቄው ውስጥ በቀጥታ ልግባና፣ ኤርትራ ላይ ያለው የድርጅትዎ ፖሊሲ በአሁኑ ጊዜ ብዙ ሰዎችን እያነጋገረ ነው፤ ከማነጋገርም አልፎ "መንግስቱ" የሚከተለውን ፖሊሲ ጥያቄ ውስጥ እያስገባ ነው። ለምንድን ነው ይህ "መንግስት" የመከላከል ፓሊሲ ይዞ ትልቅ ጥቃት እየደረሰበት፣ ጥቃቱን ተቀብሎ እየሄደ ያለው?

1ኛ/ ዘላቂና የመጨረሻ መፍትሄው ከሻአቢያ ጋር ምን ይሆናል ብለው ያስባሉ?

2ኛ/ እና የመጨረሻው ጥያቄዬ እርስዎ ወደ ኋላ ተመልሰው የተለያዩ የድርጅትዎን ፖሊሲ ቆም ብለው በማየትና በመመርመር ትልቅ ስህተት ነበር ወይንም አድርገናል የሚሉት አለ ወይ? ካለ ይህንን ማብራራት ይችላሉ ወይ? አመሰግናለሁ! Thank you አባ መላ።

ሰብሃት ነጋ፥ "እ.... ይቅርታ "ህገ-መንግስቱ" ከተናደ ትግራይ፣ አፋር የሚል passing remark ነው። "ህገ-መንግሥቱን" ፋንክሽናል እንዲሆን፣

ውጤታማ እንዲሆን ''ህገ-መንግሥቱ'' ተፈላጊ የሆኑ የሀገር ኮኒስትቲዩሽን ያው ''ህገ-መንግስቱ'' ላይ የተጠቀሱ እየተገነቡና እየተሻሻሉ መሄድ እንዳለባቸው፣ ይሄ የታግልነበት ነው። የተዋደቅንበት ነው፣ አሁንም የምንዋደቅበት ነው። እና ትግራይ ማለት ከፈረሰ ኢትዮጵያ ማለት ትግራይና ኤርትራ ማለት ትግራይና አማራ ብዬ ከሆነ ይሄ አገላለጽ ነው እንጅ ሁሉንም ይፈርሳል። ኮንስትቲሽኑም እንደማይነካ ማለት አይነካምም። እሱን ለመንካት አቅም ያለው አሁን እየተነፈሰ ነው። እየተዳከመ ነው። በኢትዮጵያ ህዝቦች እኩልነትና አንድነት የማያምን ኃይል የመምጣት እድሉ እያከተመ ነው ያለው። እንግዲህ ከመጣ ማለቴ ነው ከመጣ ግን ሁላችንም ነው የምንገነጣጠለው። ትግራይም አይቆይም፣ አፋርም አይቆይም፣ ሱማሌም አይቆይም። ማን ይቀድማል የሚለው አስተያየት የሚቀድም ትግራይ አይሆንም፣ ይሞክራል እንደገና። የመጣበት የተጓዘበት ስለሆነ። ኤኒዌይ ቻለንጅድ አይሆንም አሁን። እና ሁላችንም ለዚህ ለኢትዮጵያ ህዝቦች አንድነት መታገል ነው ያለብን። የወጣነው ይመስለኛል ዳገቱን እኔ ''በሽግግሩ ዘመን'' የወጣን ይመስለኛል። ማለት ''የሽግግሩ ዘመን'' መንግሥት ለመመሥረት የተሰበሰበ ኮንፍረንስ ያን ጊዜ ያለፍነው ዳገት ይመስለኛል። ሌሎች እንደሚመኙት በ 97 ዓ.ም በእኛ አቆጣጠር ተመኝተውት የነበረ ቢመጣ ኖሮ ማለቴ ነው፤ አሁን ያንን ያህል ሀይል ይመጣል ብዬ አልገምትም። ያኔ ኮንስትቲሽኑ ፋክሽናል ይሆናል።

ይሄ የኤርትራ ጉዳይ ያልነው እንግዲህ ማለት ሉዓላዊ ሀገር ነው። ለመወረር በእኛ በኩል የሚነሳ ነገር የለም። ማለት ፕርቮካቲብ አንሆንም። ከመጣ በቀላሉ፣ እጅግ በጣም ቀላል በሆነ መንገድ እንደሚመታ አምናለሁ። እጅግ በጣም ቀላል በሆነ መንገድ። ዋናው ግን እኔ እኛ እንደምናምነው ዋነኛው የኤርትራ ችግር ፈቺ፣ ይሄ የኤርትራ ህዝብ ነው። ውጪ ያለም ኤርትራዊ ይሁን ከአገር ቤት ያለም ኤርትራዊ። ይሄም እኔ የነበረው እየተነፈሰ ስለመጣ፣ የነበረው ትምክህት ነፋስ እየመታው ስለመጣ፣ በዚያ ላይም የተመሰረተ ስለሆነ በናሽናል ሾቭኒዝምና በሚሊተሪ አሮጋንሲ የመጣ ስለሆነ፣ ይሄ እየተሰበረ ያለ የሂደት ዳገት እንደማይወጣ እየታመነበት ስላለ፣ የመንደር የጎበዝ አለቃው፣ ሰውዬውም እየተዳከመ ውጤት የማያመጣ ግን እንደምናውቀው ሁላችን አካባቢውን በሙሉ ለመቆጣጠር የነበረ ፍላጎት ነው። የኤርትራ ችግር ሪጅናላይዝ አድርጎ፣ ሪጅናል ኢሹ ለማድረግ ነበር እና የጎበዝ አለቃውም የመንደር አለቃውም እየተነፈሰ ስላለ፣ የኤርትራን ችግር የኤርትራ ህዝብ ሩቅ ባልሆነ ጊዜ እንደሚፈታው፣ እምነታችን ነው። በዚህ ነው የሚፈታው በእኛ በኩል ወዘተ.....። '' ይላል እብሪተኛው ስብሃት ነጋ በማይጨበጥና ለመያዝ በሚያስቸግር የተለመደ ማደናጋገሪያው።

የተከበራችሁ አንባቢዎቼ ሆይ!

በተቻለኝ መጠን ጥያቄና መልሱን በሙሉ አይጋ ላይ እንደሰማሁት ነው ለማስቀመጥ የሞከርኩት። ጠያቂዎችም ሆኑ መላሹ እያንዳንዱ ቃል በቃል እንደተናገሩት ነው ያስቀመጥኩት። ምንም ነገር አልጨመርኩም። ምናልባት አንዳንድ የቃላት መዋጠች አጋጥሞኝ በደንብ ልሰማቸው ያልቻልኳቸው ካሉ (ልሰማቸው ባለመቻሌ) ካልሆነ በቀር እንዳሉ ተቸግሬ ለማስቀመት ሞክሬለሁ። እስቲ ስብሃት ነጋ ከላይ ለተጠየቃቸው ጥያቄዎች አጭበርብሬ አልፌያለሁ ብሎ

ሊሾልክ ሲል አድፍጦ ያቆሰለው ሹም፣ እንዴት ሥስ ብልቱን እንዳገኘው ለማሳየት ልሞክር።

ሹም ወደ ጥያቄው ከመሄዱ በፊት በአብሪተኛው ስብሃት ነጋ የተሰጠውን "ህገ-መግሥታችን ከተሸራረፈ" በሚል "የእንገነጣጠላለን የማስፈራሪያ ዛቻ" እዚያው ላይ ነበር አብሪተኛው ትንፋሹን ሳይቆርጥ ጠብቆ፣ በወረወረው ምትሃታዊ ቦንብ ብትስጥሱን አውጥቶ፣ የስብሃትን ድንፋታ ራቁቱን፣ ያስቀረው። "ህገ-መንግስቱ እንዳይሸራረፍ እንታገል" በሚለው ላይ እሺ እስማማለሁ፤ ነገር ግን ህገ-መንግስቱ ቢሸራረፍ/ከተሸራረፈ ትግራይ ፣ አፋር፣ ኦሮሞ ይሄዳል የሚለውን ግን አልጋራውም በማለት ነበር የስብሃት ነጋን እንዳትነኩን አሊያ እንገነጣጠላለን የሚለውን የአብሪት ጩኸቱን ቀስ አድርጎ እንዲያስተንፍሰው ለማድረግ የጣረው። የሲቪሊቲ ሩም/ክፍል ታዳሚ የሆነው ሹም፣ ለጥያቄ እድል ተሰጥቶት ወደ ጥያቄው ከመሄዱ በፊት በሰጠው ቦንብ የሆነ አስተያዬት፣ ስብሃት ባልተዘጋጀበት ሁኔታ "የትግራይ ትገነጠላለች" ዛቻውን አጽንዖት በመስጠት፣ እንዲህ ሲል አጣጥሎታል።

ሹም "ኢትዮጵያ አለ! ኢትዮጵያ ከትግራይ ውጪ፣ ትግራይ ደግሞ ከኢትዮጵያ ውጪ ይኖራሉ ብዬ እምነት የለኝም" በማለት የ75 ዓመቱን ስብሃት ነጋ አከርካሪውን በመምታት አሸመድምዶታል። እግዜር ይስጥልኝ ሹም! አንዳንዴም ትንሽ ደፍራችሁ "እንተኖችን" ስትገስጹ ከእኛ ይልቅ እናንተን በመፍራት ወደ "ሰውነት" ልትመልሷቸው ከቻላችሁ፣ አገራችሁ ኢትዮጵያን እንደአዳናችሁ ተቆጥሮ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ በሚጽፈው የታሪክ መዝገብ ውስጥ፣ እጹብ ድንቅ ቦታ ላይ ታሪካችሁ ይሰፍራል።

ሹም አስተያየቱን እጥር አድርጎ ካስቀመጠ በኋላ ወደ ጥያቄው ተመልሶ፣ የስብሃት ነጋ ድርጅት ወያኔ፣ በኤርትራ/ሻዕቢያ ላይ ያለውን የተለሳለስ አቋም በስላ ሂስ ጠርቦ "መንግስትዎ" አለ "መንግሥትዎ" እንዲህ ዓይነት ዘገምተኛና የተከላካይነት ፖሊሲ ይዞ እስከመቼ ነው የሚቀጥለው? ከኤርትራ/ሻአቢያ ጋር ያለው ችግር ዘላቂና የመጨረሻ መፍትሄውስ ምን ይሆናል ብለው ያስባሉ? ሲል ስብሃትን ወጥሮታል። በአብሪት የተወጠረው ስብሃት ነጋ እንዴት አውገርግሮና ሽውዶ ለማለፍ እንደሞከረና የማያመልጠው ጉዳይ ሲሆንበት፣ በወያኔ በኩል ብዙ ገፍቶ እንደማይሄድ ነገር ግን ከሻዕቢያ በኩል ገፍቶ ከመጣ በቀላሉ፣ እጅግ ቀላል በሆነ መንገድ "የምስራቁ ድል በሰሜኑ እንደሚደገም" በደከመ ድምጽ ሊመልስ ሞክሯል። በኛ በኩል ግን አለ ስብሃት ነጋ! በኛ በኩል የኤርትራውን ጉዳይ የኤርትራ ህዝብ ሩቅ ባልሆነ ጊዜ ሊፈታው እንደሚችል ነው ብሎ በሰለለች ድምጽ ፋይሉን ሲዘጋ ይደመጣል።

አንባቢዎቼ ሆይ!

መጀመሪያ ከላይ በሰፊው አዘበራርቆ ለመመለስ የሞከረውን ቢያስለችም፣ ትመለከቱት ዘንድ (የሀገር ጉዳይ ነውና) በትህትና እጠይቃለሁ። የሹምን 3ኛና ስብሃት ነጋ የተረሳ አስመስሎ ለማለፍ የሞከረውን ጥያቄ አባ መላ አስታውሶ ሊጠይቀው ሞክሯል። አባ መላ ያስታወሰው ጥያቄ ምን ነበር? አባ መላ በጣም አመሰግናለሁ አቶ ስብሃት! እዚህ ጋ አንድ የተዘነጋ ጥያቄ አለ። በትግሉ ታሪክ ውስጥ እርስዎ 1ኛ የድርጅቱ መስራች አንጋፋ ታጋይ ነዎት። እያንዳንዱ ትግል ውስጥ ያሉትን ነገሮች በሙሉ ያስታውሱታል። እና ወደኋላ ስያስቡት

ምንድን ነው እንዲያው አንድ መሰረታዊ የሆነ ነገር ጥፋት አጥፍተናል፣ ሪግሬት አድርገናል ብለው የሚገምቱት ነገር? ከዚህ ልምድ እንዲያው ይሄን ነገር ብናደርገው ኖሮ ጥሩ ነበረ ብላችሁ ከዚህ የተማራችሁት ትምህርት አለ ወይ? ዋነኛ ነገሩን ቢያብራሩልን?። ጉድ ነው እኮ "ሲሉ ሰምታ አሉ" ለዚህ ደግሞ ስብሃት ነጋ ምን ይመልስ ይሆን?

ስብሃት፡- ኤንወይ እ... ፋንዳሜንታል የሆነ ስህተት ነበረን ብዬ አላምንም ለብዙ ጊዜ የቆዬ።

ቂ! ቂ! ቂ! ቂ! ስቴአለሁ። የአክሱም ጽዮኗ፣ የጎንደሩ ሽህ-አብድር ይቅር የበለው። እንጅ፣ ወያኔ! ያውም ደግሞ የወያኔ ፈጣሪ ስብሃት ነጋ ተሳስቻለሁ፣ አጥፍቻለሁ ብሎ ሊናገር? የማይታሰብ። ታስቦም ከሆነ ወገኖቼ እኔ ብቻ እንዳልደከም እያንዳንዷን ከአፉ የሚያወጣትን ፊደል ሥራዬ ብላችሁ በጥሞና አዳምጡት አባካችሁ! እንዳያመልጣችሁ አደራ። እኔንም የመርዳት ያህል ነው። 'መጀመሪያ አለ ... ስብሃት ነጋ፦ እየተቸገረና ፈገግ እያለ እዚህች ላይ አዳምጡት በደንብ (ፈገግ) የምትለዋ ቃል አትገልጽልኝምና ነው "የትግራይ ሪፑብሊክ" የምትል አንድ ገጽ፣ አንድ ገጽ አይደለም አንድ ሦስት ገጽ የምትሆን፣ የተጻፈች ወረቀት ነበረች። መጀመሪያ ማለት ነው። እና ይሄ እ..እ...እ...ለተወሰኑ ቀናት ብቻ ሳይሆን በተወሰኑ ወራቶች ውስጥ ተቀዳለች። ወይይት ከተደረገባት በኋላ ማለት ነው። እ...እ....መኖሯዋን ሲሰማ አንዳንዱ የትግራይ ህዝብም ነበረ እንዴ እንደዚህ ያለ የሚል ሲሰማ፣ አንዳንድ ጊዜ አልነበረም እንለዋለን። አንዳንድ ጊዜም ማን እንደሰራት አናውቅም እንለዋለን። (ትግራይን/ኢትዮጵያን እኮ ነው ወገኖቼ።) እሷ ነበረች። እ...ነበረች ብሎ የሚያነሳው ውሸት ሆኖ ወይም ትምክህት አይደለም። ሌላ ነገር ነው። ነበረች ወይ ብሎ ለሚጠይቅ የትግራይ ህዝብ እኛ እኮ የኢትዮጵያ ቀንድ ህዝቦች ነን፣ ነበረች ይባላል የሚል ያነሳል እ...እና እሷ ነበረች አንድ ነገር..... በማለት በደንብ ሳይገልጸው አውሽልሽሎ ሊያልፈው ይሞክራል። የሚጠበቅ ነው ከስብሃት ነጋ።

ግን ወያኔ እንዴት በትግራይ ውስጥ የትግራይን ሕዝብ እያጭበረበረና በሥሩ ያሰለፋቸውን የትግራይ ህዝብ ልጆችን፣ እንዴት እየሸወደ፣ የተምታታ ታሪክ በየጊዜው እየነገረ፣ ዛሬ እነ ስብሃት ነጋና ወያኔ ለደረሱበት ሥልጣንና ኢትዮጵያን ለማጥፋት ለሸረቡት ሴራ፣ የትግራይን ልጆች እንዴት እንደማገዱ፣ በራሱ አንደበት ምስክርነት የሰጠበት ሰነድ ነው። ለዚህም ነው የትግራይን ህዝብ እስካሁን ድረስ <u>በፍርሃታቸው</u> ምክንያት አስረው፣ እንደ እቃ በጭብጣቸው ሥር አድርገው የሚያማቅቁት።

ስብሀት ነጋ ቀጥሎ ያወሳው የአፋርን ህዝብ ጉዳይ ነበር። እንዲህ ይላል ስብሃት ነጋ።

ሌላው ፖለቲካል ስህተት ሊባል የሚችለው ይልና የአፋርን እ...አፋርን ሪኮግናይዝድ አያደርግም ነበር። እንግዲህ እንደምናውቀው ሁላችን፣ የወሎ አፋር አለ፣ የትግራይ አፋር አለ፣ እና እንደ ብሄረ-ሰብ እንደ ብሄር አልቆጠርነውም። ትግራይ ማለት አፋርን ጨምሮ ነው እና የትግራይ አፋር ብለን ነበረ። እሱን ቶሎ ሰረዝነው። እና ምንድን ነው ቲ.ፒ.ኤል.ኤፍ ስናየው ኢንተርናል ድክመቶችም ነበሩት ግን ምንድን ነው የ ቲ.ፒ.ኤል.ኤፍ.ጥሩ ነገሩ ፣ ድክመቱን

በየጊዜው ያስተካክላል እንጅ ድክመቶች አልነበሩትም ማለት አይደለም። ኢንተርናሊም ድክመቶች ነበሩት። ድክመቱን በፍጥነት የማስተካከል ኢንተርናል መካኒዝም ግን አለው። ድሮም ነበረው፤ አሁንም አለው። ያ ትልቁ አሴቱ ነው። አሁን ወደ ሁለት፣ ወደ ሦስት ያልተከፋፈለ የኢትዮጵያ ድርጅት፣ ፖለቲካዊ ድርጅት አለ ከተባለ ቲ.ፒ.ኤል.ኤፍ ነው። ቲ.ፒ.ኤል.ኤፍ አይ ሃብ ኔቨር ቢን ቱ። ሁለት ሆኖ አያውቅም። የሚያፈንግጥ ይኖራል፣ ሂስቶሪካሊ ኤቨሪ 8 ይርስ (በየስምንት ዓመቱ)፣ ኤቨሪ 7 ይርስ (በየሰባት ዓመቱ) ችግር ይፈጠራል። ግን የኢንተርናል መካኒዝሙ የችግሮቹ፣ የልዩነቶቹ አፈታት አውት እስታንዲንግ ነው። የላቀ እንትን አለው የላቀ ኢንተርናል ካፓሲቲ ወዘተ...

እያለ ዛሬም ሁለት ፀጉር አውጥቶ አይኑን በጨው አጥቦ ያለ ይሉኝታ ውሸትን ራሷን ከ100 ጊዜ በላይ አጥፎ አልፏት ሄዱዋል። እንድያው የሩቁን የእነ T.L.F.(ትግራይ ነጻ አውጭ ግንባርን) በተኙበት ቀርጥፎ መብላቱን ትተን፣ የእነ አቶ አረጋዊ በረሄንና ግደይ ዘርዓጽዮንን አወጣጥ ረስተን፣ የእነ ታምራት ላይኔን "በስኳዋር መቃም" መቀመቅ መውረድ ትተን፣ የእነ ክነፈ ገ/መድህንን "በወስላታ" መገደል ዘንግተን፣ የእነ ሃየሎምን "በስካራም እጅ" እድሜው ማጠሩን አስታውሰን፣ የእነ ስዬ አብራሃምን "በነቀዘ ሙስና" የኢትዮጵያን ሀብት ዘርፎ የከርቸሌ ቤተኛ መሆንን ረስተን፣ የአባይ ጸሃየን "ከአፈንጋጮች" ጋር ሲያውደልድል፣ በወያኔ አውት ስታዲግ የልዩነቶች መፍቻ "መካኒዝም" የመለስን ጨማ ስሞ ምኅረት የተደረገለትን አያየን፣ ዓለም ሁሉ የእነ ስብሃት ነጋን የችግር መፍቻ ቁልፍ አለመዋሱ፣ እንዴት ያሳዝናል!!!። እንዲህ አይነት ትንግርት የሆነ፣ "ለትውልድ" ተጽፎ መተላለፍ ያለበትን የወያኔን ድንቅ "አሴት" እኔ መግለጫ ስለሌለኝ አሁንም እንደለመድኩት ከሊቀች ጽሁፍ አንዱዋን ተውሸ፣ ነገሬን ልዘጋ ፈቀድኩ። ክፍል ሶስትን በሚቀጥለው ይዤ ብቅ እላለሁ።

"በየፖለቲካው መስክ የሚቧርቅ ውሸት፣ የራሱ ዓይነትና ይዘታዊ ባህርይ ሲኖረው በአብዛኛው ሥልጣንና ኃይላዊ ጉልበት ላይ (Authority & power) የሚሽከረከር ውሸት ነው። ለሥልጣን የሚቋምጥ ግለ-ሰብ ወይም ቡድን "ከእኔ በላይ ላሳር ነው"በሚል ዘዴ "ከሰማያት የወረድኩ ልዩ ፍጡር ነኝ" እስከማለት ድረስ ያስቀባጥረዋል። ከመሰሉም ፍጡር የተለየ ለመምሰል "ደሜ ሐምራዊ ቀለም ነው" ብሎ እስከ መዘላበድ ድረስ ያቃዠዋል። "ትውልዴም ባለ ሺ ጅማት ከላቸው ከነእንቶኔ ዘርያ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ነው" እስከማለትም ድረስ ያስቀላምደዋል። ለዚህ ዐይነት የባለ-ውሸት አበጋዝ፣ ብዙ ስመ-ጥርና ዕውቅ አምባገነኖችን በናሙናነት ማቅረብ ይቻላል። በሶሻልና በኢኮኖሚውም የህይወት እንቅስቃሴ ውስጥ፣ የየዐይነታቸውን ባሕሪ የሚያንጸባርቁ አያሌ ምሳሌዎችን ማቅረብ፣ ይቻላል። ትንሽ ዘረዘር አርገን በዘመናችን የሚከናወኑትን ዐይን አውጣ ውሸቶችን ብንጠቃቅስ፣ ከፖለቲካ ጋር የቅርብ ተዛምዶ ያለውን የፕሮፓጋንዳ ውሸት መጥቀሱ እጅግ አርኪ ነው። ባልነበረ ጦር ሜዳና ባልዘመተ ሠራዊት ባዶ ሁኔታ ላይ፣ የድል ቅዠት ያወፈፈው ቡድን፣ ድንገት ተነሥቶ " ሺ ሰዎች ማረኩሁ፣ ዘመናይ መሳሪያዎችን በገፍ ማረክሁ፣ ሺ ገደልኩ፣ ጉጡርጡራ የተባለውን ልዩ ለጦር አመች ቦታ፣ ከጠላት አስልቀቄ ከጇ አገባሁ..." በማለት ደረቅ ቱልቱላውን ይነፋል። የሚገርመው ደግሞ የራሱ ተዋጊዎች ልዩ የእቃቤ-ርዕስ (ጥይት የማያስመታ) መድኃኒትና አስማት ያላቸው ይመስል ከዚያ ሁሉ ወራሪ ሰራዊቱ ውስጥ፣ ያን ያህል ከፍተኛ ጀብዱ ሲያደርግ አንድም እንኳ መሞት ቀርቶ ያልቆሰበት መሆኑን አለመግለጹ፣ ነው። ይህ ዓይነቱ የጦርነት ግብግብ ውሸት፣ በዘመኑ ቋንቋ "ፀሊም ፕሮፓጋንዳ" (Black propaganda)

> ወይም "አሳሳች ዜና" (disinformation) ተብሎ ይጠራል።አሥር ተዋጊዎችን ምርኮ አስገብቶ እንደሆነ አሥሩን በአሥር ያባዛና መቶ ተዋጊዎች ማርኬያለሁ ሲል፣ ይፎሽካል። የትልቅ ከተማ ጎረቤት የሆነች የገጠር መንደር የያዘ እንደሆነ፣ ዋናውን ከተማ በቁጥጥሬ ሥር አርጌያለሁ ሲል፣ ጣቃውን ይቀዳል። ከዋሹ አይቀር እንዲህ ቅልጥልጥ ብሎ እንጂ። በተራ ጆሮዎች በኩል አሟልጬ ለመግባት እንዲያስችል!!"

(እሳት ጠፋ! ይበል?) ከ ኃይሉ ገ/ዮሐንስ ገሞራው የተውሰደ። አመሰግናለሁ! ጋሼ ሃይሉ (ገሞራው) ለተቸገርኩበት የስብሃት ነጋ ቅጥ ያጣ ቅጥፈት፣ ትክክለኛውን መግለጫ ከመጽሐፍህ አገኘሁ። አቦ! እንኳንም የኢትዮጵያ ልጅ ሆንክ!
ቸር ይግጠመን!!

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!